# የተሰጠኝን እውቅና ፍፁም የምኩራራበት ሳይሆን ለበለጠ ሥራ እንድተጋ የተጣለብኝ አደራ አድርጌ ነው የምቆጥረው::

## Professor Getnet Tadele



### “እኔ በትምህርት ያገኘኋቸውን ጥሩ ነገሮች ሌሎችም እንዲያገኙ ጽኑዕ ምኞት አለኝ”

**ጥር 8 ቀን 2015 ዓ.ም**

ተወልደው ያደጉት በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር አዘና ወረዳ፣ ዶጌን በምትባል አነስተኛ መንደር ውስጥ ነው:: ከትውልድ መንደራቸው በእግር የ40 ደቂቃ መንገድ ተጉዘው ትምህርታቸውን የጀመሩት የዚህ እትም እንግዳችን ከትምህርት ጋር ተያይዞ ያለፉበት መንገድ በውጣ ውረድ የተሞላ ነው:: ያን ውጣ ውረድ አልፈው አሁን ላይ ለትልቅ ደረጃ በቅተዋል::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዘና ከተታተሉ በኋላ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ግምጃ ቤት ተምረዋል:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመማር ከትውልድ መንደራቸው 65 ኪሎ ሜትር ርቀት ወደ ዳንግላ ከተማ ለመሄድ የተገደዱት እንግዳችን ዳንግላ በሚያውቋቸው ሰው ቤት በመኖር የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን አጠናቀዋል::

አሥራ ሁለተኛ ክፍል ባመጡት ጥሩ ውጤት መሰረት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ ተምረው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ይዘዋል:: በዚያው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአስተማሪነት ሥራ የጀመሩት እንግዳችን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ

ከሀገረ አውስትራሊያ ተቀብለዋል:: ከአውስትራሊያ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከያዙ በኋላ ሦስተኛ ዲግሪያቸውን ከኔዘርላንድ ባገኙት የትምህርት እድል መሠረት ተምረው አጠናቀዋል:: አሁንም ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ሙሉ ፕሮፌሰር ናቸው:: ለምርምር እና ጥናት ወደ በርካታ ሀገራት የተጓዙት ፕሮፌሰሩ በሀገር ውስጥ ደግሞ የገጠር ትምህርት ቤቶችን በማስገንባት፣ ድልድይ በማሠራት እና በሌሎችም ዘርፎች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የተወጡ ምሁር ናቸው:: በማስተማር፣ ምርምሮችን በማካሄድ፣ ተተኪ ምሁራንን በማፍራት፣ የበጀት ድጋፎችን በማስገኘት፣ የበጐ ሰው ሽልማት በማግኘት እና በሌሎችም መልካም ተግባሮቻቸው ከሚታወቁት ፕሮፌሰር ጌትነት ታደለ ጋር የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሳን ቆይታ አድርገናል::

መልካም ንባብ!

እስኪ የትምህርት ጉዞዎን ይግለጹልን…

እንደ አጋጣሚ ሆኖ እኔ የተወለድኩበት መንደር እና የነበረው ትምህርት ቤት ብዙም የተራራቁ አልነበሩም:: ከቤቴ እስከ ትምህርት ቤቱ ያለው መንገድ በእግር ከ40 ደቂቃ በላይ የሚወስድም አልነበረም:: ችግሩ ግን ከቤታችን እስከ ትምህርት ቤቱ ባለው መንገድ መሀል አንድ ትልቅ ወንዝ መኖሩ ነው::

በቤተሰባችን ውስጥ የተማረ እና ትልቅ በታ ላይ የደረሰ አንድም ሰው ባለመኖሩ ምክንያት ትምህርት ቤት ገብቼ የመማሬ ምክንያት በወቅቱ ግልጽ አልሆነልኝም:: ያም ቢሆን ግን ትምህርቴን ጀምሬያለሁ:: የእናቴ ወንድም ከእኔ ቀድሞ ትምህርት ቤት የገባ የቤተሰባችን አባል ቢሆንም ትምህርቱን ከአምስተኛ ክፍል አቋርጦ ነጋዴ በመሆኑ እኔ የትምህርትን ጥቅም የምረዳበት አንዳችም ምክንያት አልነበረኝም::

ወላጆቼ ምንም እንኳን ትምህርቴን እንድማር ቢፈቅዱልኝም ከትምህርቴ ይልቅ ትዳር መስርቼ፣ ቤት ሠርቼ፣ ልጆች ወልጄ እና ሌሎች የገጠር ልጆች በሚያድጉበት መንገድ አድጌ ጥሩ አርሶ አደር እንድሆን እንጂ በትምህርቴ ብዙ ርቀት እንድጓዝ አልፈለጉም ነበር:: ያም ሆኖ ግን የኔ የትምህርት ጉዞ እና ስኬት ለሌሎች የገጠር ልጆች ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ ፈጣሪ ፈቃዱ በመሆኑ አሁን ለደረስኩበት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ለመብቃት ችያለሁ::

በዚያ የልጅነት ጊዜዬ የትምህርት ጥቅም ሳይገባኝ፣ ሚኒስትሪ እና ማትሪክ ስለሚባሉት ፈተናዎች ሳላውቅ ራሴን በአዘና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ አግኝቼዋለሁ:: በወቅቱ የተማረ ሰው የሚባለው የሚያገኘው የሥራ ዕድል አስተማሪነት ሲሆን ለአስተማሪዎች የሚሰጠው ክብርም ትልቅ ነበር::

የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ከትውልድ መንደሬ በ17 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ግምጃ ቤት ከተማ ተምሬያለሁ:: ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን የተከታተልኩት ደግሞ ከመንደራችን 65 ኪሎ ሜትር በምትርቀው የዳንግላ ከተማ ነው:: የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የመለስተኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአካባቢያችን አለመኖራቸው ነው::

ግምጃ ቤት እና ዳንግላ ትምህርቴን ስማር ከቤተሰቦቼ ርቄ የሄድኩ በመሆኑ የምኖረው በሚያውቁኝ ሰዎች ቤት ውስጥ ተከራይቼ ነበር:: ኪራይ ሲባል ደግሞ እንዳሁኑ ለብቻ አንድ ክፍል መያዝ ሳይሆን ጠዋት ጠላ ሲሸጥበት በሚውል ቤት ውስጥ ማታ መደብ ላይ ወይም መሬት ላይ ተኝቶ ማደር ነው::

አዘና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን ስማር ከአንደኛ ክፍል ወደ ሦስተኛ ክፍል እና ከሦስተኛ ክፍል ደግሞ ወደ አምስተኛ ክፍል ሁለት ክፍሎችን በአንዴ አልፌያለሁ:: ስድስተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ልንፈተን ስንል ለመጀመሪያ ጊዜ ፎቶ ግራፍ መነሳቴንም አልዘነጋውም:: ወደ አየሁ እርሻ ልማት በመጡት ትራክተሮች ላይ መሳፈር ምን ያህል ብርቅ እንደሆነብኝ እና ስድስተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ተፈትኜ ባመጣሁት ጥሩ ውጤት ምክንያት ወደ ግምጃ ቤት ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴ ሄጄ መዘናጋቴንም ፈጽሞ አልረሳውም::

በደርግ መንግሥት ስድስተኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ለመሠረተ ትምህርት መዝመት እንደሚችሉ እና በወር 40 ብር ይከፈላቸው እንደነበረም ስለማውቅ ለመዝመት ሳመለክት መዝጋቢው ልጅነቴን አይቶ አባርሮኛል:: ሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ላይ ከትምህርቴ ብዘናጋም ስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ያመጣሁት ውጤት ጥሩ ነበር:: ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ግን ለትምህርቴ ትኩረት መስጠት እና ራሴንም ጐበዝ ነኝ ብዬ ማሳመን ጀምሬያለሁ::

ዳንግላ 11ኛ እና 12ኛ ክፍልን ስማር አንደኛ ወጥቻለሁ:: በአሥራ ሁለተኛ ክፍል የመልቀቂያ ፈተናም በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ለዩኒቨርሲቲ የሚያበቃ ውጤት አምጥቻለሁ:: በውጤቴ መሠረትም በመጀመሪያ ምርጫዬ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቼም በሶሾሎጂ በጥሩ ውጤት ዲግሪዬን ይዣለሁ:: ከዚያ በኋላ ከአውስትራሊያ ሁለተኛ እና ከኔዘርላንድ ደግሞ ሦስተኛ ዲግሪዬን በጥሩ ውጤት አግኝቻለሁ::

በኔዘርላንድ ሦስተኛ ዲግሪዬን በአራት ዓመት ውስጥ በማጠናቀቄ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ዩሮ ተሸልሜያለሁ:: ይህ የሆነው በአብዛኛው ተማሪ በአማካይ ሦስተኛ ዲግሪውን የሚያጠናቅቀው በስድስት እና ከዚያም በላይ ዓመታት በመሆኑ ነው::

ከዶክትርነቴ በኋላ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕርግ ያገኘሁትም በአንፃሩ በጥሩ ዕድሜ ላይ በነበርኩበት ወቅት ነው::

በሀገራችን በርካታ ምርምሮች ቢደረጉም የዝቅተኛውን ማኅበረሰብ ችግሮች ሲፈቱ አይታዩም፤ ለምን ይሆን?

ለዚህ ችግር አንድ ሦስት ምክንያቶችን ማንሳት እችላለሁ:: የመጀመሪያው ጥናቶች ወይም አጀንዳው በማን ነው የሚቀረፀው? የሚለው ነው:: ጥናቱን የሚቀርፁት ገንዘብ ያላቸው ሀገራት እና ተቋማት ናቸው:: ጥናቶቹ የሚያተኩሩት ደግሞ ጥናቱን ባዘጋጀው አካል ፍላጎት ላይ ነው:: በዚህ አይነት ጥናቶች ውስጥ የተመራማሪው ወይም አጥኚው ሚና የጎላ አይሆንም:: ጥናቱም ችግር የማይፈታ ሊሆን ይችላል::

ሁለተኛው ችግር ደግሞ የኛ የተመራማሪዎች ነው:: የምንሠራቸው ምርምሮች የኅብረተሰብ ችግሮችን መነሻ ያደረጉ ናቸው ወይ? ኅብረተሰቡን በሚገባው ቋንቋ ነው ወይ ምርምሮችን የምናካሂደው? ምርምሮቻችን ኅብረተሰብ አሳታፊ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ለራሳችን ማቅረብ ይኖርብናል:: እኔን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች ምርምሮቻችንን የምንሠራው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው:: የሚታተሙትም በታወቁ ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ የምርምር መጽሔቶች ላይ ነው::

ተመራማሪዎች የምናሳትማቸው የምርምር ጽሑፎች የራሳችንን የተመራማሪዎቹን እድገት የሚወስኑ መሆን አለመሆናቸውን እንጂ "የኅብረተሱን ችግር ምን ያህል ይፈታሉ?" በሚለው አናተኩርም:: የምርምር ጽሑፎች መመዘኛ በራሱ በምርምሩ ችግር ፈቺነት ላይ አያተኩርም:: ተመራማሪዎችም ብንሆን የምርምር ሥራዎቻችን በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ወደ ሕዝቡ እንዲደርሱ አናደርግም::

ሦስተኛው ችግር ደግሞ ከፖሊሲ አውጪዎች እና ከፖሊሲ ፈፃሚዎች አንፃር የሚታይ ነው:: ብዙውን ጊዜ በኛ ሀገር እውቀት የሚመነጨው ከሥልጣን ነው:: ሥልጣን ያለው ሰው እውቀት ባይኖረውም በምርምር እና ጥናቶች ላይ ውሳኔ ያሳልፋል:: ሚዲያዎችም ቢሆኑ በአንዳንድ ትላልቅ መድረኮች ላይ ጥናት አቅራቢው ወይም ባለሙያው ካቀረበው ጥናት ይልቅ ባለሥልጣኖች ለተናገሩት ነገር የበለጠ ትኩረት ይሰጣሉ:: የዜና ርዕሳቸውም የተመራማሪው ጥናት ሳይሆን የባለሥልጣኑ ንግግር ይሆናል:: ይሄ ብዙዎቻችን ሥልጣን እና እውቀት ምን ያህል እንደተምታቱብን አንዱ ማሳያ ነው::

የተጠኑ ጥናቶች እያሉ እና ውጤታማ አለመሆናቸውን እያየን ሌሎች ጥናቶች መልሶ የማስጠናት ችግሮችም ይስተዋሉብናል:: ሁሌ ሥልጠና ማካሄድ እና ዐውደ ጥናቶችን መክፈት ብቻውን ውጤታማ አያደርግም:: ያ ማለት ግን ሁሉም ጥናቶች እርባና ቢስ ናቸው ማለት አይደለም:: በተለያዩ ዘርፎች የተሠሩ አንዳንድ ጥናቶች ውጤታማ ሲሆኑም አይተናል:: በአብዛኛው ግን ውስንነቶች እንደሚታዩ አስተውያለሁ::

ጥናቶች እና ምርምሮች ውጤታማ እንዲሆኑ ከማን ምን ይጠበቃል?

መንግሥት እና ኅብረተሰቡ ለጥናት እና ምርምሮች ዋጋ መስጠት አለባቸው:: በተለይ መንግሥት በተጨባጭ ለሚታዩ የኅብረተሰብ ችግሮች ጥናት ማካሄጃ በጀት መመደብ ይኖርበታል:: ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በሚፈለጉ አጀንዳዎች እንጂ ማንም በሚቀርጽልን አጀንዳ መመራት አይኖርብንም:: አጥኚዎችም በተቻለ መጠን ጥናቶቻቸው ወደ ታች ወርደው የኅብረተሰብን ሕይወት በሚለውጡበት መንገድ ላይ መሠራት ይኖርባቸዋል::

ዩኒቨርሲቲዎች የእውቀት እና የምርምር ማዕከል መሆናቸውን በተጨባጭ ማረጋገጥ ያሻል:: አንዳንድ ጥናቶች በባህርያቸው ችግር መፍታት የሚችሉ ናቸው:: አንዳንዶቹ ደግሞ እውቀትን ያሳድጋሉ:: ሁለቱንም አይነት ጥናቶች በአግባቡ ልንጠቀምባቸው ይገባናል:: የብዙኀን መገናኛዎችም ጥናቶች ወደ ኅብረተሰቡ እንዲወርዱ በማድረግ ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል:: በጥናቶቻችን ለአብነት የግብርናውን ዘርፍ ስናይ "ለምንድን ነው እስካሁን በበሬ የምናርስ? ለምንስ ነው ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎች ያላደጉት? እንዴት የገበሬውን ሕይወት ቀላል እናድርግለት? እንዴትስ ምርታማ እናድርገው?" እያልን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል:: ይሄ በግብርናው ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዘርፎች መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው:: "የሀገራችን ሰላም እንዴት ይስፈን?" የሚለውም ልዩ ትኩረት እና ጥናት ሊደረግበት ይገባል::

ከምርምር እና ጥናቶች ጋር በተያያዘ የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮ እንዴት ይገፁታል?

ለትምህርት እና ለሥራ በተመላለስኩባቸው የውጭ ሀገራት ባየሁት መሠረት መንግሥት ለዜጐቹ ልዩ ክብር አለው:: መንግሥት የዜጐችን ጥያቄ በአግባቡ ከመመለሱም በተጨማሪ ዜጐቹ ለሚያቀርቡለት ጥያቄም ሆነ ከዜጐቹ ለሚሰጡት አስተያየቶች በጐ ምላሽ መስጠትን እንደ ባህል አድርጎታል:: ይሄንኑ ጉዳይ ከኛ ሀገር አንፃር እንየው ብንል ብዙ ነገሮች ልክ አይደሉም::

መንግሥት አብዛኞቹን ምሁራን የሚያያቸው የሥርዓቱ ተቺ እንደሆኑ አድርጐ ነው:: ምሁራን እና ሌሎች ዜጐችም መንግሥትን ሥልጣን ፈላጊ ብቻ አድርገው ያዩታል:: እነዚህ አተያዮች መቀየር አለባቸው:: እንደ ምዕራባዊያኑ ሀገራት መንግሥት እና ዜጐች ተቀራርበው መሥራት አለባቸው:: መንግሥት እና ዜጐች መከባበርም ይኖርባቸዋል:: ግብር መክፈል፣ ሰላምን ማስፈን እና መሰል ነገሮች ተግባራዊ የሚሆኑት መንግሥት እና ዜጐች ሲከባበሩ እና ሲተማመኑ ነው:: እነዚህ ነገሮች ሲኖሩ ምርምር እና ጥናቶች የኅብረተሰብን ችግሮች ፈቺ ሊሆኑ ይችላሉ::

ባደጉበት አካባቢ ትምህርት ቤቶችን፤ ድልድይ እና ቤተ መጽሐፎችን አስገንብተዋል፤ ሌሎችንም ሥራዎች ሠርተዋል:: የእነዚህ በጐ ተግባሮችዎ ምንጫቸው ምን ይሆን?

መነሻው በሰው ስቃይ የምታመም መሆኔ ነው፤ በሰው ችግርም እቸገራለሁ:: እንደ አብነት ዳንግላ ሁለተኛ ደረጃ እየተማርኩ በትምህርታቸው ከኔ የሚያንሱ ልጆችን አስተምር ነበር:: ዩኒቨርሲቲ ገብቼም ዐይነ ስውራን ተማሪዎች ሲፈተኑ በበጐ ፈቃደኝነት

ፈተናውን አነብላቸው ነበር:: በኬኔዲ ቤተ መጽሐፍት ውስጥም የማስጠናቸው እና መጽሐፍትን እያነበብኩላቸው በቴፕ ቀድቼላቸው የሚያጠኑ ዐይነ ስውራን ተማሪዎችም ነበሩ::
እኔ ያደኩት ከአዘና ሻገር ብላ ባለች መንደር ውስጥ በመሆኑ ወደ አዘና ለመምጣት ትልቁን የአየሁ ወንዝ መሻገር የግድ ይለኛል:: የአየሁ ወንዝ በተለይ በክረምት ሰዎችን ይበላል:: ወንዙ ላይ የነበረው የእንጨት ድልድይ ባህላዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለመሻገር በእጅጉ የሚያስቸግር ነው:: በወንዙ የተበሉ ሰዎችን አስከሬን መፈለግ፣ ጥይት መተኮስ፣ ዋይታ እና ለቅሶ የአካባቢዉ የዘወትር ችግር መሆኑን እያየሁ ነው ያደኩት::
የዚህ ወንዝ ሙላት እና ተያያዥ ችግሮች ብዙ ናቸው:: የኛ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን /አቡነ ዘር አብሩክ/ ከወንዙ ማዶ ያለ በመሆኑ በክረምት ቤተ ክርስቲያን መሳለም፣ የሞተ መቅበር እንዲሁም ገበያ መሄድ አንችልም:: ወላዶች ወደ ህክምና መሄድ አይችሉም:: በዚህ ወንዝ ምክንያት በክረምት የሚለያየው የማኅበረሰብ ክፍል ብዙ ነው::
ያደኩት ይህንን ችግር እያየሁ ነው:: ሦስተኛ ዲግሪዬን ጨርሼ ከኔዘርላንድ እንደተመለስኩ የአየሁ ወንዝን የሚያሻግር ድልድይ ለመሥራት አሰብኩ:: እኔ ባለፍኩበት ችግር አሁንም ድረስ እየተሰቃዩ ያሉ ወገኖቼን ለማገዝ ወሰንኩ:: በውሳኔዬ መሰረትም ድልድዩን ለመገንባት የሚያስችል እቅድ አቅጄ ከ200 ለሚበልጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች በተንኩ:: ወቅቱ 1997 ስለነበር የፖለቲካዉ ትኩሳት ሊሆን ይችላል ለጥሪዬ ምላሽ የሚሰጠኝ አካል ማግኘት አልቻልኩኝም::
ተስፋ ግን አልቆረጥኩም:: ማኅበራዊ ገፆችን ስፈትሽ አንድ የካናዳ ድርጅት ድልድይ እንደሚሠራ አወኩ:: ጥያቄዬንም አቀርብኩላቸው:: የድርጅቱ ኃላፊ በእርግጥም ድርጅቱ ድልድዮችን እና ትምህርት ቤቶችን እንደሚሠራ ገለጸልኝ:: ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ድልድይ እንዲሠራላቸው የሚጠይቁት የችግሩ ባለቤቶች እንጂ እንደኔ ከችግሩ የራቀ ሰው አለመሆኑን ነግሮኝ ከብዙ ውይይቶች፣ ጥናቶች እና ውጣ ውረዶች በኋላ ድልድዩ በ2009 ለመሠራት በቅቷል:: የአካባቢዬን ማኅበረሰብ ባለኝ አቅም ሁሉ መደገፍ የጀመርኩትም ከዚህ ድልድይ ግንባታ በኋላ ነው::
የትምህርት ቤቶችን ግንባታ የጀመርኩትም በልጅነቴ በአካባቢዬ ትምህርት ቤት በማጣት ያሳለፍኩትን መጥፎ ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብዬ በማየት ነው:: እኔ ከአዘና ግምጃ ቤት፣ ከግምጃ ቤት ደግሞ ዳንግላ ለትምህርት ስሄድ የመማር አቅም አጥተው የቀሩ ብዙ ጎበዝ ተማሪ ጓደኞቼን አስታውሳለሁ:: በዚህም ምክንያት የአዘናን ትምህርት ቤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት /አስፈላጊውን ነገሮች ሁሉ እንዲሟሉለት በማድረግ/ እንዲያድግ ማድረግ ችያለሁ::
በአዘና ሌላ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በግምጃ ቤት የሁለተኛ ደረጃ ማስፋፊያ እና ተጨማሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አሠርተናል:: ከዚህ በኋላ በየዓመቱ እኔ ያመጣሁት ረጂ ድርጅት ትምህርት ቤቶችን እየገነባ እና እያስፋፋ የአካባቢውን የትምህርት ሽፋን በእጅጉ እንዲጨምር ማድረግ ተችሏል:: በትምህርት ቤቶች አለመኖር ምክንያት የማይማሩ ልጆች እንዳይኖሩ በማድረግም ሀሳቤን በከፊል ማሳካት ችያለሁ::
በትምህርት ቤቶች ረገድ ከ10 ያላነሱ ፕሮጀክቶችን እውን አድርጌያለሁ:: ወደፊትም የምሠራቸው ብዙ ሥራዎች ይኖሩኛል:: ትምህርት ለኔ ልዩ ስጦታዬ ነው:: እኔ በትምህርት ያገኘሁትን ጥሩ ነገር ሌሎችም እንዲያገኙ ጽኑዕ ምኞት አለኝ:: መስጠት ለህሊና የሚፈጥረው እርካታ ከምንም በላይ ነው::
በማኅበራዊ ጥናት ዘርፍ የዓመቱ በጐ ሰው መባልዎ ምን ስሜት ፈጠረብዎ?
በጐ ሰው መባል ይከብዳል:: እኔም በጐ ሰው ነኝ ብዬ አላምንም:: ነገር ግን ሽልማቱን የሰጠኝ አካል የሠራኋቸው ሥራዎች ለሀገር ያላቸውን ፋይዳ በማጤን ጥሩ ነው ብሎ ሸልሞኛል::
እኔ በጐ ሰው ከመባሌ ይልቅ ለሥራዬ እውቅና በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ:: ነገር ግን የተሰጠኝን እውቅና ፍፁም የምኩራራበት ሳይሆን ለበለጠ ሥራ እንድተጋ የተጣለብኝ አደራ አድርጌ ነው የምቆጥረው:: የዚህ እውቅና ሌላው ጠቀሜታ ሌሎች የሚሠሩ ሰዎችን ማበረታታቱ ነው::
ሰዎች በሕይወት እያሉ ለሠሩት ሥራ እውቅና ሲሰጣቸው ለበለጠ ሥራ ይነሳሳሉ:: እኔ ባቀረብኳቸው ሌሎች ጥናቶችም የክብር ከፍተኛ ሎሬት የሚል ሽልማት ከአቢሲኒያ ተሰጥቶኛል:: ለእኔ ከምንም በላይ ትልቅ ሽልማት ነው የምለው በምሠራቸው ሥራዎች ኅብረተሰቡ ደስታን አግኝቶ ማየቴ ነው:: አዘና ላይ በስሜ የሚጠራው ትምህርት ቤትም ለእኔ ከፍተኛ የሕዝብ ሽልማት ነው::
ቀረ የሚሉት መልዕክት ካለዎት?
ለአሥራ አምስት ዓመታት በዘለቀው የማኅበራዊ ተሳትፎዬ ምንም እንኳን የኔ ስም በጉልህ ይጠራ እንጂ እኔ ብቻዬን ያደረኩት ነገር እንደሌለ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ:: ኅብረተሰቡን፣ የረዱኝን የተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦችን ጭምር ማመስገን እፈልጋለሁ:: በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በኔዘርላንድ፣ በአውስትራሊያ፣ በእንግሊዝ፣ በደቡብ አፍሪካ እና በሌሎችም ሀገራት የምትገኙ ተቋማት እና የሥራ አጋዥ ጓደኞቼ በኔ ስኬት ውስጥ የእናንተም አሻራ አለበት እና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ማለት እፈልጋለሁ::
ከጋዜጣችን ጋር ለነበረዎት ቆይታ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን!
እኔም ለተሰጠኝ እድል ከልቤ አመሰግናለሁ!

(እሱባለው ይርጋ)
በኲር ጥር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዕትም
በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ዘወትር ሰኞ የምትታተመውን የበኲር ጋዜጣን ሙሉ ፒዲኤፍ
በhttp://www.amharaweb.com/Bekur ላይ ማግኘት ይችላሉ።

https://www.facebook.com/100069774588547/posts/pfbid022CsLyZmJMrweK1Ddv5DfbFJYUfj6RheT3u1HLkyUpxXYrcDmVi8cBBpsN9LaVSz7l/?mibextid=Nif5oz